EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መቀላቀል ኢሞራላዊ ተግባር ብቻ ሳይሆን በወንጀል የሚያስጠይቅ ነው!

ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መቀላቀል ወይም መከለስ በተለይ በዓላትን አስታኮ የሚስተዋል ቢመስለም ሁኔታውን ልብ ላለ ግን ለአንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች የሡርክ ተግባራቸው ነው:: ስኳርን ከማር ጋር ቅቤን ከሙዝ፣ሩዝን ከጤፍ ጋር በመቀላቀል የተጀመረው ሕገወጥ ድርጊት ዛሬ ላይ ለማየትና ለመስማት በሚከብድ ሁኔታ በርበሬን ከሸክላ ፣ጤፍን ከጀሶ ማር ከግራሶ፣ ቅቤ ምንነቱ ካልታወቀ ባዕድ ነገር፣ በርበሬ ከሠጋቱራና ከማቅለሚያ ጋር፣ ዘይትን ከሸንት ጋር በመቀላቀል የከፋታቸውን ጥግ በማይታመን ሁኔታ አሳድገውታል::

ይህን መሰሉ ኢሞራላዊ ድርጊቶችን የሚፈፅሙ ጥቂት የማይባሉ በአፍቅሮተ ነዋይ የታወሩ ነጋዴዎች ድርጊታቸውና የከፋታቸው አይነትና ብዛት ዛሬ ዛሬ ሲብስ እንጂ ሲቀንስ እምብዛም አይታይም:: ‹‹ለምን?›› ለሚለው ጥያቄ ጥናትን መሰረት ያደረገ አመክንዮ ያለው ምላሽ የሚጠይቅ ቢሆንም በዛሬ ጽሑፋችን ግን ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መቀላቀል ወይም መከለስ በጤና፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚ ሕይወታችን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እንዳስሳለን::

ምግብ መከለስ / Food Adulteration/ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ላይ ሌላ ባዕድ ነገር በመጨመር ወይም ይዘቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይም በተገቢው መንገድ በንጽህና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ ነው:: የምግብ ክለሳ /Food adulteration/ የምግቡን ጣዕም፣ ተፈጥሮአዊ ይዘትና መጠኑን በመቀየር የምግቡን ጥራትና ደህንነት በከፍተኛ ሁኔታ ለብልሽት ይዳርጋል::

የምግብ ክለሳ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ሲሆን ያልተገባ ጥቅም ለማካበት በማሰብ ወይም በቸልተኝነት ወይም በማምረት፣በማከማቸት፣በማጓጓዝ እና ለሽያጭ በማቅረብ ሂደት ውስጥ ተገቢውን የጥረትና ደህንነት ጥንቃቄ ባለማድረግ ሊከሰት ይችላል:: ይህንን ተከትሎም ተጠቃሚው ህብረተሰብ ለመታለል፣ ለመጭበርበር ወይም ለጤና መጓደል/ለህመም/ሊጋለጥ ይችላል::

በአጠቃላይ የምግብ ክላሳ ወይም መቀላቀል ድርጊትን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን:: ሆን ተብሎ የሚደረግ ክለሳና በቸልተኝነት የሚደረግ ክላሳ በማለት:: ሆን ተብሎ የሚደረግ ክለሳ /Intentional /Deliberate / ይህ ዓይነቱ የክለሳ ሂደት የሚከሰተው አምራቾች ወይም ነጋዴዎች ትርፋማነትን ለማሳደግ በአቋራጭ ለመክበር ሲባል አፍቃሬ ነዋይ ያለባቸው፣ ተአማኒነት የጎደላቸው የሚያደርጉት ድርጊት ነው:: ሰብአዊነትን ወደ ጎን በመተው እና ገንዘብን የሚያስቀድሙ ናቸው:: ለዚህ ዓላማቸውም በተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶች ውስጥ እንደ ዱቄት ፣ውሃ፣ ስኳር፣ ሙዝ፣ የአትክልት ዘይት፣አፈር፣የጠመኔ ዱቄት፣ሞላሰስ፣ተቆልቶ የተፈጨ የገብስ ዱቄት ወ.ዘ.ተ ሌላ ባዕድ የሆኑ ነገሮችን ደባልቆ የመከለስ ተግባር እንዲሁም ምግቦች ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ንጥረ ምግቦችን /Nutrients-Food/ በማስወገድ የሚፈፅምበት በመሆኑ ሆን ተብሎ ከማይፈፀም ክለሳ /Adulteration/ እጅግ አስከፊው ያደርገዋል::

ሌላው በቸልተኝነት የሚደረግ ክለሳ /accidental Adulteration/ ተብሎ የሚጠራው ይህ አይነቱ ክለሳ የሚከሰተው አምራቾች ወይም ነጋዴዎች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ብለው በሚያደርጉት ጥረት ሳይሆን ምርትን አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ሂደት ውስጥ መደረግ በሚኖርበት ጥንቃቄ ላይ ጉድለት መኖር ነው: : በማምረት፣በማከማቸት፣በማጓጓዝ ለሽያጭ በማቅረብ ሂደት የሚፈጠር ነው:: በሀገራችን እንደየአከባቢው ሁኔታ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶችና መጠጦች ለባዕድ ነገር ክለሳ/Adulteration/ የተጋለጡ ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ እንደ ማር፣ቅቤ፣ወተትና የወተት ውጤቶች፣ጤፍ፣ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣በርበሬና እንጀራ ምርቶች ላይ እምነት አሳድሮ መገብየት የማይቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል::

የምግብ ክለሳ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች/ impact of Food Adulteration / ካየን ቀዳሚው በአንድ ሀገር ላይ የማህበራዊ፣የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ውድቀት የሚያስከትል ሲሆን በመቀጠልም የሚጨመሩ ባዕድ ነገሮች ምግቡን በመመረዝ ወይም አጠቃላይ የምግቡን ይዘትና መጠን ለብልሽት በማጋለጥ የሰው ልጅ በሚመገብበት ወቅት ከፍተኛ የጤና መታወክ ያስከትላሉ:: ካንሰር፣ አላርጂክ፣ ተቅማጥ፣ አስም የመሳሰሉ ከባድ በሽታዎች ያስከትላሉ::

የምግብ ክላሳ በህብረተሰባችን ላይ የሚያደርሰው አደጋ በመገንዘብ መንግሥት ከምግብ ጋር ባዕድ ነገር በሚቀላቅሉ አካላት ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት እንደሚወሰድባቸው በአዋጅ አስቀምጧል:: በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጁ ቁጥር 11/2011 ላይ ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት መከለስ፣ ደረጃውን የማያሟላ ማድረግና በሰው ጤና ላይ ጉዳት ማድረስ፣ ባዕድ ነገር መቀላቀል፣ መመረዝ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በብር 500 ሺ ብር ያስቀጣል:: በሰው ላይ ሞት ካስከተለ ደግሞ በ20 ዓመት ጽኑ እስራትና በብር ከ30ሺ እስከ 400ሺ ብር ቅጣት ተቀምጧል:: በዚህ አግባብም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በርካቶች በዚህ ህገወጥ ድርጊታቸው ተከታትሎ በመያዝ እንዲቀጡ እያደረገ ይገኛል::

የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እንደሚያመለክተውም በምግብ ላይ ባዕድ ነገር መጨመር እንደስፋቱና እንዳደረሰው ጉዳት አይነት ቅጣት ተጥሎበታል። ከዚያ ያለፈ ችግር ካደረሰም በወንጀል ህጉም እንዲታይ እድል ሰጥቷል::

ስለሆነም የንግድ እንቅስቃሴ ማደግን ተከትሎ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አንዳንድ ምርቶች ምንጫቸው ያልታወቀ፣ ከባዕድ ነገር ጋር የተደባለቁ እንዲሁም የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ የምግብ ምርቶች ላይ ስለሚደረግ ባዕድ ነገር ክለሳ/Food adulteration/ የክለሳ ዓይነቶች እና በሸማቹ ህብረተሰብ ላይ ሊያስከትላቸው ስለሚችለው ተያያዥ ችግሮች ተመጋቢው ህብረተሰብ እንዲገነዘበው ማድረግ ያስፈልጋል::

ሕብረተሰቡን በምግብ ደህንነት ከሚከሰቱ የምግብ ወለድ በሽታዎችና ሌሎች በምግብ ብክለት ከሚከሰቱ ችግሮች ለመከላከል መንግሥት በአዋጅ 661/2002 እና በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 189/2002 ለመቆጣጠር ለኢ.ም.መ.ጤ.ክ.አ.ቁ.ባለስልጣን ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን፤ ለሰው ጤናና ደህንነት አደገኛ የሆነ፣ምንጩ ያልታወቀ፣የጥራት ደረጃው የወረደ፣ወይም የተመረዘ፣የአገልግሎት ጊዜው ያለፈ ወይም ከባእድ ነገሮች ጋር የተደባለቀ የንግድ ዕቃን ወይም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም መሸጥ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር መሆኑን በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ይደነግጋል።።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በየጊዜው በሚያደርገው ቁጥጥርና ክትትል ቅቤ፣ በርበሬ፣ ማር ወተትና እንጀራ ከባዕድ ነገር ጋር ተቀላቅለው ተገኝተዋል:: ስለሆነም ባለሥልጣኑ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ ኅብረተሰቡ ለራሱ ደኅንነት ሲል ሊሳተፍ ይገባል፤ ስለሚመገበው ምግብ መጠየቅ መጀመርና ጥፋተኞችን ተባብሮ በማጋለጥ መሰል ጥርጣሬዎች ሲኖሩት በአካባቢው ለሚገኙ ተቆጣጣሪ አካላት ጥቆማ እንዲያደርግና ወንጀል የሚፈጽሙ አካላት ለህግ እንዲቀርቡ ሀገራዊ ግዴታውን እንዲወጣ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን::

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ